አምሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
52nd Year — No. 41

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም.
Addis Ababa, 20th May 1993

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት
ነጋሪት ጋዜጣ
NEGARIT GAZETA
OF THE TRANSITIONAL GOVERNMENT OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ 1·30

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ

የፖስታ ሣጥን ቁ. ፹ሺ፩ (80,001)

ማውጫ

ቁጥር ፶፩/፲፱፻፹፭ ዓ. ም.
ለኤርትራ ማቋቋሚያና መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ . . ገጽ ፫፻፷፮

CONTENTS

Proclamation No. 51/1993

International Development Association Credit Agreement for partly for financing the Rehabilitation and Reconstruction Project of Eritrea Ratification Proclamation . . . . Page 366

አዋጅ ቁጥር ፶፩/፲፱፻፹፭ ዓ.ም.

ኢትዮጵያ መንግሥትና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ...ል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ

አዋጅ

ለኤርትራ ማቋቋሚያ መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ከፊል ...ፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ. ዲ. አር ፲፰ ሚሊዮን ፩፻ ... (ኤስ. ዲ. አር አሥራ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ) ... ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ...ግሥትና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል መጋ...ት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. በዋሽንግተን ዲሲ ስለተፈረመ

በዚሁ የብድር ስምምነት መሠረት የሚገኘው የብድር ...ዘብ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥትና በኤርትራ ጊዜያዊ ...ግሥት መካከል በተፈረመ የመልሶ ማበደር ስምምነት ...ሠረት ለኤርትራ መልሶ ማቋቋሚያና ግንባታ ስለሚውልና ...ርትራ መንግሥትም በብድሩ ስምምነት መሠረት ለዓለም ...ቀፍ የልማት ማኅበር መፈጸም ያለባቸውን ግዴታዎች የሚ...ጽም ስለሆነ ፤ ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ የሽግ...ር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቀው ስለሆነ ፤ ...ሽግግሩ ወቅት ቻርተር አንቀጽ ፱/መ/እና/ሸ/መሠረት የሚ...ለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ « ለኤርትራ ማቋቋሚያና መልሶ ግንባታ ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፶፩/፲፱፻፹፭ » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

PROCLAMATION NO. 51/1993

A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

Whereas, a Credit Agreement between the Government of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Government of Ethiopia a credit in various currencies equivalent to eighteen million one hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 18,100,000) was signed in Washington D.C. on the 7th day of April 1993;

Whereas, the credit obtained under the Credit Agreement is to be utilized for the rehabilitation and reconstruction of Eritrea through a Subsidiary Loan Agreement concluded between the Transitional Government of Ethiopia and the Provisional Government of Eritrea pursuant to which Eritrea assumes the obligations owned to the International Development Association under the said Credit Agreement;

Whereas, said Credit Agreement has been ratified by the Council of Representatives of the Transitional Government of Ethiopia;

Now Therefore, in accordance with Article 9(d) and (h) of the Transitional Period Charter, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for partly financing the Rehabilitation and Reconstruction Project of Eritrea Ratification Proclamation No. 51/1993"

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ « የብድር ስምምነት » ማለት በኢትዮጵያ መንግሥትና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው ።

፫. የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትር በብድሩ ስምምነት የተገኘውን መጠኑ ኤስ. ዲ. አር ፲፰ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ (ኤስ. ዲ. አር አሥራ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ) የሆነውን ገንዘብ በብድሩ ስምምነት በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ. ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamaiton "Credit Agreem
Agreement signed in Washington
April 1993 between the Governmen
International Development Associati

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby
take all acts necessary for the uti
amounting to SDR 18,100,000 (SDR
hundred thousand) in accordance w
conditions set forth in the Credit Agre

4. *Effective Date*

This proclamation shall enter into fo
publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 20th day

MELES ZENAWI

PRESIDENT OF THE TRANSITIONA
OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING PRESS

ሃምሳ ሁለተኛ ዓመት ቍጥር ፵፪
52nd Year — No. 42

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም.
Addis Ababa, 23rd June 1993

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

ነጋሪት ጋዜጣ

NEGARIT GAZETA

OF THE TRANSITIONAL GOVERNMENT OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ 0.60	በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክርቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖስታ ሣጥን ቍ.፹ሺ፩ (80,001)

ማውጫ

ፖ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ ዓ.ም:

የማዕድን አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ ዓ.ም. . ገጽ ፫፻፷፰

CONTENTS

Proclamation No. 52/1993

Mining Proclamation No. 52/1993 ....Page 368

አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ ዓ.ም.

ማዕድን ሀብት ልማትን ለማስፋፋት የወጣ አዋጅ

የማዕድን ሀብት ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛ አስ ፅኦ ያለው የሕዝብ ሀብት በመሆኑና የዚህም ሀብት ጥበ ና ለሕዝቡ ጥቅም መዋል በመንግሥት መረጋገጥ ያለበት ሆኑ ፤

የማዕድን ሀብት ፍለጋ ፣ ምርመራና ማምረት ሥራ በተ ው ቴክኖሎጂና የሀብት ጥበቃ መሠረተ ሐሳቦች በመመ ት መካሄድ እንዳለበት እና ለማዕድን ኢንዱስትሪ የሚያ ለገውን የሙያ ዕውቀት በሀገር ውስጥ እንዲዳብር ማበ ታት ማስፈለጉን በመገንዘብ ፤

የግል ኢንቨስትመንት ለልማቱ አስፈላጊ የሆነውን ካፒ ል ፣ ቴክኖሎጂና ገበያ በማስገኘት ረገድ ሊጫወት የሚ ለውን ከፍተኛ ሚና በመረዳት ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የማዕድን ሥራዎችን ተመለከተ አዲስ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ ፱/መ/መሠ ት የሚከተለው ታውጅዋል ።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ « የማዕድን አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

PROCLAMATION NO. 52/1993

A PROCLAMATION TO PROMOTE THE DEVELOPMENT OF MINERAL RESOURCES

WHEREAS, all mineral resources are public property which have a significant contribution to the economic development of the country and that the state shall ensure the conservation and development of the resources for the benefit of the people;

WHEREAS, prospecting, exploration and exploitation of mineral resources should be carried out in accordance with appropriate technology and sound principles of resource conservation and develop national expertise in the mining industry; and

WHEREAS, recognizing the significant role of private investment in the capital formation, technology acquisition and marketing of minerals;

WHEREAS, to achieve these ends it is essential to promulgate a new law on mining operations;

NOW, THEREFORE, in accordance with article 9 (d) of the Transitional Period Charter of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART I.

GENERAL

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Mining Proclamation No. 52/1993."

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩. «ስምምነት» ማለት በመንግሥትና በባለፈቃድ መካከል ማዕድናትን ለመፈለግ ፣ ለመመርመርና ለማምረት የሚደረግ ውል ነው ፤

፪. «ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ» ማለት ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር በሞተር ኃይል በማይንቀሳቀስ መሣሪያ እየታገዘ አብዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወን ሆኖ በኢትዮጵያውያን የሚካሄድ የወርቅ ፣ የፕላቲንየምና ሌሎች የከበሩ ማዕድናት ፣ የብረት ፣ የጨው ፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉት ማዕድናት የማምረት ሥራ ነው ፤

፫. «የኮንስትራክሽን ማዕድን » ማለት አብነበረድ ፣ ግራናይት ፣ ባዛልት ፣ አሸዋ ፣ ጠጠር ፣ ድንጋይ ፣ የሸክላ አፈር የመሳሰሉት እና ሌሎች ሚኒስትሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸው ብረት ነክ ያልሆኑ ማዕድናት የሚያጠቃልል ነው ፤

፬. «ኮንትሮለር» ማለት የማዕድን ሥራዎችን ለመቆጣጠር በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የተመደበ ባለሥልጣን ነው ፤

፭. «ክምችት» ማለት በገፀ ምድር ላይ ወይም በከርሰ ምድር ውስጥ በአንድ በተወሰነ ሥፍራ በተፈጥሮ የሚገኝ ማናቸውም የማዕድን ስብስብ ነው ፤

፮. «መመርመር» ማለት አንድን ክምችት ፈልጐ ለማግኘት ፣ ለመገምገም እና ለመመዘን የማዕድናትንም ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ባሕሪያት ለማጥናት እንዲሁም ክምችቱ ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ሊለማና ሊመረት ስለመቻሉ ከከርሰ ምድር ጂኦሎጂና አወቃቀር ፣ ከምድር ቁፋሮ፣ ጥልቅና ጥልቅ ያልሆኑ የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ጂኦሎጂያዊ ፣ ጂኦፊዚካላዊ ፣ ጂኦኬሚካላዊ እና የመሳሰሉ ከርሰ ምድርን ለማወቅ የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚደረግ ማንኛውም ተግባር ነው ፤

፯. «መንግሥት» ማለት እንደአግባቡ ማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ወይም ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድር ነው ፤

፰. «ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ» ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት ከፍተኛ ደረጃ ተብሎ የሚሰየም የማዕድን ማምረት ሥራ ነው ፤

፱. «ፈቃድ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የማዕድናትን የመፈለግ ፣ የመመርመር ወይም የማምረቻ ፈቃድ ነው ፤

፲. «የፈቃድ ክልል » ማለት ማናቸውም ፈቃድ የተሰጠበት ሥፍራ ነው ፤

፲፩. «ፈቃድ ሰጭ ባለሥልጣን » ማለት የብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር የማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ወይም እንደአግባቡ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤

2. *Definitions*

In this Proclamation unless the context provides other-wise:

1. "agreement" means a contract between the Government and a licensee in order to prospect, explore and mine for minerals;
2. "artisanal mining" means, unless otherwise specified by directive issued by the Minister, non-mechanized mining operations of gold, platinum, precious minerals, metals, salt, clay, and other similar minerals of an essentially manual nature carried out by Ethiopian individuals or groups of such persons;
3. "construction minerals" means sand, gravel, stone (marble, granite, basalt etc) clay including non-metallic minerals used for construction purpose and such other minerals as the Minister may, by directive so designate;
4. "controller" means an officer authorized by the Licensing Authority to control Mining Operations;
5. "deposit" means any natural concentration of minerals found on or within a specified area of the earth's crust;
6. "to explore" means to undertake all acts to search for, appraise and evaluate a deposit, by using different methods of studies /geological, geochemical and geophysical/relating to subsurface geology and structure, excavation, boring and drilling, analysis of the physical and chemical properties of minerals and examination of the economic feasibility of developing and producing a deposit;
7. "Government" means the Central Transitional Government or the National/Regional Transitional Self-Government, as may be appropriate;
8. "large-scale mining" means any mining operation be designated as such by the Minister in accordance with regulations to be issued for implementing this Proclamation;
9. "license" means a license issued pursuant to this Proclamation to prospect, explore or mine for minerals;
10. "License area" means any area which is the subject of a License;
11. "Licensing Authority" means the Mines and Energy Bureau of the National/Regional Self-Government for artisanal mining and construction minerals mining carried out by domestic investors and Ministry of Mines and Energy for the rest of mining operations

፲፪. «ማምረት» ማለት ማዕድናትን ለማልማት ፣ ለመለየትና ከክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ሲሆን ማዕድናትን ማከማቸትን ፣ ማዘጋጀትን ወይም ፕሮሴስ ማድረግን ፣ ማጓጓዝንና መሸጥን የሚያካትት ሲሆን ማቅለጥንና ማጣራትን አይጨምርም ፤

፲፫. «የማዕድን ውኃ» ማለት ለጤንነት ተስማሚነት ያላቸውን ማዕድናት የያዘ ውኃ እንዲሁም ማዕድናት ከውስጡ ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ተለይተው ሊወጡ የሚችሉበት እንደብራይን ያለ ውኃ ነው ፤

፲፬. «ማዕድን» ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው የምድር ክፍል ሆኖ ወይም በምድር ላይ ወይም ውስጥ በተፈጥሮ ተከማችቶ የሚገኝ ሲሆን ጨውን ፣ የማዕድን ውኃንና የጂኦተርማል ክምችትን ይጨምራል ፤ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፹፮ አንቀጽ ፪/፯/ በተመለከተው ትርጓሜ የተሸፈነውን ነዳጅ (ፔትሮሊየም) አይጨምርም ፤

፲፭. «ሚኒስትር» እና «ሚኒስቴር» ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትርና ሚኒስቴር ነው ፤

፲፮. «የማዕድን ሥራዎች» ማለት ማዕድናትን ለመፈለግ፣ ለመመርመርና ለማምረት የሚካሄድ ማንኛውም ተግባር ነው ፤

፲፯. «ሰው» ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ፤

፲፰. «የከበሩ ማዕድናት» ማለት እንደ ፕላቲንየም ፣ ወርቅና ብር የመሳሰሉ የከበሩ ብረታ ብረት ፣ እንደ አልማዝ ፣ ሩቢ ፣ ኢመራልድና ሳፋየር ያሉ የከበሩ ድንጋዮች እንዲሁም ሚኒስትሩ በመመሪያ የከበሩ ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸው ሌሎች ተመሳሳይ ማዕድናት ናቸው ፤

፲፱. «መፈለግ» ማለት ማዕድናት ሊኖሩ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ፣ የመሬትን ጂኦሎጂና አወቃቀር ባሕርያት ማጥናትን ጨምሮ የማዕድን ምልክቶችን በመፈለግ በገጸ ምድር ላይና ከገጸ ምድር በላይ የሚካሄድ ማናቸውም ተግባር ነው ፤

፳. «አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ» ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት አነስተኛ ደረጃ ተብሎ የሚሰየም የማዕድን ማምረት ሥራ ነው ።

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚካሄድ ማናቸውም የማዕድን ሥራ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ።

ክ ፍ ል ሁ ለ ት
ስለ ማዕድን ሀብቶች
ምዕራፍ አንድ
ጠ ቅ ላ ላ

፬. የፈቃድ አስፈላጊነት

፩. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፣ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳/፩/ እና አንቀጽ ፳፩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የጸና ፈቃድ ሳይኖረው የማዕድን ፍለጋ፣ ምርመራ ወይም ማምረት ሥራ ሊያካሂድ አይችልም ።

12. "to mine" means to undertake all acts to develop, extract and remove minerals from a deposit, including their storage, treatment, processing (excluding smelting and refining), transportation and/or disposal;

13. "mineral water" means water containing minerals with healthful properties and water such as brines from which minerals may be extracted on an economic basis;

14. "minerals" means any naturally occurring mineral substance of economic value forming part of or found on or within the earth's crust, including salt, mineral water and geothermal deposits, but excluding petroleum, natural gas and oil shale as defined in article 2(7) of Proclamation No. 295/1986;

15. "Minister" and "Ministry" means the Minister and the Ministry of Mines and Energy, respectively;

16. "Mining Operations" means all acts carried out to prospect, explore and mine for minerals;

17. "person" means any natural or legal person;

18. "precious minerals" means precious metals such as platinum, gold and silver and precious stones such as diamonds, rubies, emeralds and sapphires and such other minerals as the Minister may, by directive so designate;

19. "to prospect" means to undertake on or above the surface of the earth all acts to search for mineral occurrences in order to ascertain the possible presence of minerals including the geological and structural characteristics of the land;

20. "Small-scale mining" means mining operations to be designated as such by the Minister in accordance with regulations to be issued for implementing this Proclamation.

3. *Scope of Application*

This Proclamation shall apply to and govern the conduct of all operations and related activities within the territory of Ethiopia.

PART II
MINING RIGHTS
CHAPTER I
GENERAL

4. *Requirements of Mining Rights*

1. Without prejudice to sub-article 2 of this Article, Articles 20(1) and 21 of this Proclamation, no person shall prospect, explore or mine unless he is a holder of a license.

፪. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፍለጋ ፈቃድ ባይኖረውም የአንድን ባለፈቃድ ወይም የሌላ ሰው መብት ሳይነካ ማዕድን መፈለግ ይችላል ።

፭. **ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል ሰው፣ በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተገለጹትን መሠረታዊ ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የገንዘብ ምንጭ፣ የቴክኒክ ችሎታ፣ ሙያና ልምድ ያለው ከሆነ ፈቃድ ሊያገኝ ይችላል ።

፪. ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ለማግኘት የገንዘብ ምንጭ፣ የቴክኒክ ችሎታ፣ ሙያና ልምድ አይጠይቅም ።

፫. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭/፪/ ከተደነገገው በስተቀር ፈቃድ የተሰረዘበት ሰው ፈቃዱ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ለአምስት ዓመታት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም ።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገውን የሚያሟሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በፈቃድ አሰጣጥ ረገድ ቅድሚያ ይኖራቸዋል ።

፮. **ስለተያዙና ስለተከለከሉ ሥፍራዎች**

መንግሥት ማንኛውንም ሥፍራ ለተወሰነ የማዕድን ሥራ ለመያዝ እንዲሁም በማንኛውም ሥፍራ በተለይም በታሪካዊ፣ በባህላዊ ወይም በሃይማኖት ሥፍራዎች፣ በሕዝብ አገልግሎት ሕንፃዎች፣ በመሠረተ ልማቶች እና በሌሎች ተቋማት አካባቢ የማዕድን ሥራዎች እንዳይካሄዱ ሊከለክል ይችላል ።

፯. **በመንግሥት ስለሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች**

መንግሥት ለጠቅላላ ኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን የማዕድን ሥራዎች በራሱ ወይም ከግል ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት ሊያካሂድ ይችላል ።

ምዕራፍ ሁለት
ቅድመ ልማት መብቶች
ንዑስ ክፍል አንድ
ፍለጋ

፰. **የፍለጋ ፈቃድ**

፩. የፍለጋ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ የተመለከቱትን ማዕድናት በፈቃዱ ክልል ውስጥ መፈለግ የሚያስችል ብቸኛ የሆነ መብት ይሰጣል ። የፍለጋ ፈቃድ ሊተላለፍ፣ ሊደረግ፣ ዋስ ሊሆን ወይም በውርስ ሊተላለፍ አይችልም ።

፪. የፍለጋ ፈቃድ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ሲሆን ሊታደስ አይችልም ።

፫. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ላይ የተመለከቱት ማዕድናት በፈቃድ ክልል ውስጥ ለመኖራቸው ምልክት ካገኘ፤ እና

2. Any Ethiopian may prospect without a prospecti[ng] license, provided he does not interfere in any w[ay] with the rights of a licensee or any other perso[n].

5. *Eligibility for Mining Rights*

1. Without prejudice to sub-article 2 of this Artic[le] any person, who satisfies the requirements of lice[nse] set out in this Proclamation, regulati[ons] and directives to be issued under this Proclamati[on] may acquire a license provided that he is qualifi[ed] to carry on trade under the provisions of the Co[m]mercial Code and possessing the required financ[ial] resources, technical competence, professional s[kill] and experience necessary to fulfill the obligati[ons] under the license.

2. No person is required to possess financial resour[ces,] technical competence, professional skill and ex[pe]rience in order to acquire artisanal mining lice[nse.]

3. No person whose license has been revoked except provided for under Article 15(2) of this Procla[ma]tion may hold another license for 5 years follow[ing] such revocation.

4. Domestic investors who fulfil all requirements [pro]vided under sub-article 1 of this Article shall [have] priority in acquiring license.

6. *Reserved and Excluded Areas and Minerals*

The Government may, designate any area of minera[ls] reserved or excluded for particular mining opera[tions] and exclude any area from mining operations particu[larly] as regards sites of historical, cultural or religious int[erest] and public buildings, infrastructure and other installat[ions].

7. *Government Mining Operations*

The Government may undertake some mining opera[tions] that are vital for overall economic growth either by [itself] or in partnership with private investors.

CHAPTER 2
PRE-DEVELOPMENT RIGHTS
SECTION 1
PROSPECTING

8. *Prospecting License*

1. A prospecting license grants an exclusive righ[t to] prospect for the minerals within the license [area.] Prospecting license may not be transferred, assi[gned,] encumbered or inherited.

2. A prospecting license is valid for a period of one [year] and may not be renewed.

3. Upon his discovery of indications of minerals [speci]fied in the license within the license area, the [licen]see shall have the right to be granted an explo[ration] license, provided that,

ሀ) በፍለጋ ፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈጸመ ፤

ለ) ለምርመራ ፈቃድ የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላ ፣

ሐ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የፍለጋ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በቀር ፤ የምርመራ ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል ።

ንዑስ ክፍል ሁለት
ስለምርመራ

የምርመራ ፈቃድ

፩. የምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ የተመለከቱትን ማዕድናት በፈቃዱ ክልል ውስጥ ለመመርመር የሚያስችል ብቸኛ የሆነ መብት ይሰጣል ።

፪. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር የፈቃዱ ክልል ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት አመቺ የጂኦሜትሪ ቅርጽ ይኖረዋል ።

፫. የምርመራ ፈቃዱ በዕዳ ሊያዝ ወይም በውርስ ሊተላለፍ አይችልም ፡ ሆኖም ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ የምርመራ ፈቃዱና የባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲/፫/ መሠረት የማምረት ፈቃድ የማግኘት መብት ሊተላለፍ ወይም ሊዳረግ ይችላል ።

ለምርመራ ፈቃድ ዘመንና ዕድሳት

፩. የምርመራ ፈቃድ በመጀመሪያ ለሦስት ዓመታት የሚያገለግል ሆኖ ሁለት ጊዜ ለአንድ አንድ ዓመት ሊታደስ ይችላል ። ባለፈቃዱ ተጨማሪ የላቀ የምርመራ ተግባር ማከናወን እንደሚያስፈልግ ካስረዳ ወይም ለፈቃድ ዘመኑ መራዘም በቂ ምክንያት የሚሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች ስለመኖራቸው መረጃ ካቀረበ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተጨማሪ ዕድሳት ሊፈቅድ ይችላል ።

፪. ባለፈቃዱ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈጸመ ለዕድሳት የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል ።

፫. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል ውስጥ የሚገኝ በፈቃዱ ላይ የተመለከተ ማዕድናት ክምችት ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ሊመረት መቻሉን ካረጋገጠ ፤ እና

ሀ) በምርመራ ፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ፤ ሟላ ፣

ለ) ለማምረት የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላ ፣

a) he has fulfilled all obligations under the prospecting license;

b) meets all requirements in connection with the application for an exploration license; and

c) he is not in breach of any provisions of this Proclamation, regulations or directives issued hereunder which constitutes grounds for suspension or revocation of the prospecting license.

SECTION 2
EXPLORATION

9. *Exploration License*

1. An exploration license grants an exclusive right to explore for the minerals within the area specified in the license.

2. The license area shall, unless the Licensing Authority specifies otherwise, be of simple geometric form, as specified by directive issued by the Minister.

3. An exploration license may not be encumbered or inherited, but the license and the licensee's right to obtain a mining license pursuant to Article 10 sub-article 3 of this Proclamation may be transferred or asisgned with the prior approval of the Licensing Authority.

10. *Duration and Renewal*

1. An exploration license is valid for an initial period of three years and may be renewed twice for additional terms of one year each. The Licensing Authority may further allow extension of renewal periods where the licensee documents the necessity for additional advanced exploration activity, or provides information on other circumstances which justify an extension of the duration of the license.

2. The licensee shall have the right to renew the license, provided he has fulfilled the obligations specified in the license, meets all requirements in connection with the application for the renewal and is not in breach of any provision of this Proclamation which constitutes grounds for suspension or revocation of the license.

3. The licensee shall have the right to be granted a small-scale or large-scale mining license in the event that he determines a deposit of the minerals specified in the license within the license area may be mined on an economically viable basis, provided that, he:

a) has fulfilled all obligations under the exploration license;

b) meets all requirements in connection with the application for such a mining license; and

ሐ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የምርመራ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በቀር ፣ አነስተኛ ወይም ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል ።

፲፩. ከፈቃድ ክልል ላይ የተወሰነውን ስለመልቀቅ

፩. የምርመራ ፈቃድ እንዲታደስለት የሚጠይቅ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው የመሬት ክልል ከሩብ እጅ የማያንስውን ሥፍራ የሚለቅ መሆኑን ማመልከት አለበት።

፪. የሚለቀቁ ሥፍራዎች ቅርጽ ፣ አቀማመጥና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናሉ ።

ንዑስ ክፍል ሦስት

ስለ ግኝት

፲፪. ግኝትን ስለማስታወቅ

የማዕድናትን መኖር ወይም ምልክት ያገኘ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ የግኝቱን ቦታና ባሕርይ ለኮንትሮለሩ በጽሑፍ መግለጽ አለበት ።

፲፫. ስለቅድሚያ መብት

፩. ማንኛውም ባለፈቃድ ያልሆነ ሰው ቀድም ሲል መኖራቸው የማይታወቅ የማዕድናትን ምልክት ወይም ክምችትን ካገኘ እንዲሁም ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ ያልተመለከቱ ወይም በፈቃዱ ክልል ውስጥ ያልሆኑ እና ቀደም ሲል መኖራቸው የማይታወቅ ማዕድናትን ምልክት ወይም ክምችት ካገኘ የማዕድናቱ ምልክት በተገኘበት ሥፍራ ወይም የክምችቱ ቦታ ሊሆን በሚችለው ክልል ላይ ወዲያውኑ ምልክት ማድረግ አለበት ።

፪. ማዕድናቱና ክልሉ ብቸኛ የሆነ መብት የሚያስገኝ ፈቃድ የተሰጠባቸው ወይም በሌላ ሁኔታ የተያዙ ወይም የተከለከሉ ካልሆነ አግኚው የምርመራ ወይም የማምረት ፈቃድ የማግኘት ቅድሚያ መብት ይኖረዋል ።

ይህም ሲሆን ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የግኝቱ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ጸንቶ የሚቆይ ግኝት ሰርቲፊኬት ለአገኘው ይሰጠዋል ። በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የግኝት ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው የምርመራ ወይም የማምረት ሥራ ለማካሄድ የሚያስችለውን የገንዘብና የቴክኒክ ችሎታ ለማሟላት አስፈላጊውን ዝግጅት ሊያደርግ ወይም ኮንትሮለሩን አስቀድሞ በማስፈቀድ መብቱን ለሶስተኛ ወገን ሊሰጥ ወይም ሊያስተላልፍ ይችላል ።

c) is not in breach of any provisions of this Proc[...] mation, regulation or directives issued hereun[...] which would constitute grounds for suspen[...] or revocation of the exploration license.

11. *Relinquishment of Portion of License area*

1. In applying for each renewal of an exploration li[...] se, the licensee shall indicate the portion of the lic[...] se area, to be relinquished, which shall not be l[...] than one quarter of the original license area.

2. The form, orientation and other details regardi[...] relinquishments shall be specified by directive iss[...] by the Minister.

SECTION 3

DISCOVERY

12. *Notification of Discoveries*

Any person who discovers indications or existence [...] minerals shall immediately notify the controller in writ[...] the location and nature of such discovery.

13. *Preferential Right*

1. Any person who is not a licensee in an area where [...] discovers indications or a deposit of minerals wh[...] were not previously discovered and any licensee w[...] discovers indications or a deposit of minerals wh[...] are not specified in the license or which are not [...] cated within the license area and which were [...] previously discovered shall immediately mark [...] location of the indication of the minerals or the lik[...] boundary of the deposit.

2. If the minerals and the area in question are [...] subject to an exclusive license or have been exclu[...] or reserved, the discoverer shall have a preferen[...] right to obtain an exploration or a mining lice[...] thereon. In such event, the Licensing Authority s[...] immediately issue a Discovery Certificate Valid fo[...] period of one year from the date of notification of [...] discovery. During such period the discoverer [...] seek to acquire the financial and technical capabi[...] necessary to explore and/or to mine for the mine[...] in question or he may assign or transfer such ri[...] to a third party with a prior approval of the contr[...] ler.

የግኝት ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው አግባብ ላለው የፈቃድ ማመልከቻ የሚጠየቁትን ተፈላጊ ሁኔታ ዎች ሲያሟላ የተገኙትን ማዕድናት በተመለከተ እንደነገሩ ሁኔታ የምርመራ ወይም የማምረት ወይም ሁለቱንም ያጣመረ ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል ፤ የግኝት ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው ባለፈቃድ ከሆነ የቀድሞው ፈቃዱ የተገኙትን ማዕ ድናት ወይም አዋሳኝ የሆነውን ክልል እንዲጨ ምር ተደርጐ እንዲሻሻልለት በአማራጭነት የመጠ የቅ መብት ይኖረዋል ፤ ሆኖም የተሻሻለው ክልል ሊፈቀድ ከሚችለው ክልል ጣሪያ ሊያልፍ አይች ልም ።

ምዕራፍ ሶስት

ስለ ልማት መብቶች

ንዑስ ክፍል አንድ

ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ

ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ

፩. ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ የተመለከተውን ማዕድን በፈቃዱ ክልል ውስጥ የመ መርመርና የማምረት ብቸኛ የሆነ መብት ይሰጣል። ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ከ፲፭ ሜትር የማ ይበልጥ ወደ መሬት ውስጥ በቀጥታ ከሚደረግ ቁፋሮ በስተቀር የተነሌንግና ሌሎች ከመሬት በታች የሚካሄዱ ሥራዎችን አይጨምርም ።

፪. ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ፈቃድ ሰጭ ውን ባለሥልጣን በማስፈቀድ ለሌሎች ሊተላለፍ ሊዳረግ ፣ በዕዳ ሊያዝ ወይም በውርስ ሊተላለፍ ይችላል ።

ስለፈቃድ ዘመንና ዕድሳት

፩. ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለአንድ ዓመት የሚያገለግል ሆኖ ለተመሳሳይ ጊዜ ያለገ ደብ ሊታደስ ይችላል ።

፪. የክምችቱን ኢኮኖሚያዊ አለኝታ በተሻለ ሁኔታ ለማልማት የላቁ የምርመራና የማምረት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ሲታመንበት ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የ፺ ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀ ቂያ በቅድሚያ በመስጠት ባሕላዊ የማዕድን ማም ረት ሥራ ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል ።

፫. ባለፈቃዱ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን በላቀ የምርመራና የማምረት ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚያስፈልገው የቴክኒክ ብቃትና የገ ንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማሳየት ከቻለ የቅድሚያ መብት ይሰጠዋል ።

፬. ባለፈቃዱ የቅድሚያ መብት የማይሰጠው ሲሆን በፈቃዱ መሰረዝ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳይ ሊከፈለው የሚገባውን የካሣ መጠን ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ይወስናል ። ይህም ካሣ ለባለፈቃዱ በተፋጠነ ጊዜ ውስጥ ይከፈለዋል ።

3. The holder of a Discovery Certificate shall have the right to be granted an exploration or a mining or a combined exploration/mining license, as the case may be, with regard to such minerals, and a holder of a discovery certificate who is a licensee shall, alternatively, have the right to be granted an amendment to the license to include the discovered minerals or area adjacent to his existing licence, provided that the amended license area doesn't exceed the maximum allowable area and provided that he meets all requirements pertaining to the relevant application.

CHAPTER 3

DEVELOPMENT RIGHTS

SECTION 1

ARTISANAL MINING

14. *Artisanal Mining License*

1. An artisanal mining license grants an exclusive right to explore and mine for the minerals within the license area. Artisanal mining operations shall exclude all tunnelling and other underground work except vertical excavations of less than fifteen meters in depth.

2. An artisanal mining license may be transferred, assigned, encumbered or inherited, subject to the approval of the Licensing Authority.

15. *Duration and Renewal*

1. An artisanal mining license shall be valid for one year and may be renewed indefinitely for like periods.

2. The Licensing Authority may, after giving 90 days prior written notice, cancel an artisanal mining license where it is considered that the deposit requires more advanced exploration and mining method for the best development of its economic potential.

3. The Licensing Authority shall give preferential treatment to the licensee where the latter shows that he has the necessary technical and financial resources to engage in the advanced exploration and mining as prescribed by the Licensing Authority.

4. Where preferential treatment is not accorded to the licensee, the Licensing Authority shall determine the amount of compensation which shall be paid to the licensee for the loss he incurred due to the cancellation of the license. Such compensation shall be paid to the licensee promptly.

ንዑስ ክፍል ሁለት

አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ

፲፮. ስለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ

፩. አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ማዕድናት በፈቃዱ ክልል ውስጥ የማምረት ብቸኛ የሆነ መብት ይሰጣል ። ፈቃዱ የማዕድን ሥራውን ለማካሄድ በቂ ይሆናል ተብሎ በሚገመት ደረጃ አስፈላጊ የሆነውን ክልል የሚሸፍን ይሆናል ፤ የክልሉ ወሰንና ቅርጽ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል ።

፪. የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ ለሌሎች ማስተላለፍ ፣ መያዣ ወይም በዕዳ ማስያዝ ይቻላል ። እንዲሁም የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ፈቃዱ በውርስ ሊተላለፍ ይችላል ፤ ሆኖም ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳይፈቅድ ውርሱ የፈቃዱን ክልል መከፋፈልን የሚያስከትል ሊሆን አይችልም በተጨማሪም የማዕድን ሥራው በዚህ ምክንያት ከዘጠና ቀናት በላይ ተቋርጦ ቢቆይ ፈቃዱን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ይሆናል ።

፲፯. ስለፈቃድ ዘመንና ዕድሳት

፩. የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ቢበዛ ለአሥር ዓመት ወይም የክምችቱ ዕድሜ ከአሥር ዓመት በታች ከሆነ ለዚሁ ዘመን የሚያገለግል ይሆናል ። ፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል ።

፪ ባለፈቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ካሟላና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል ።

ንዑስ ክፍል ሶስት

ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ

፲፰. ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ

፩. ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ማዕድናት በፈቃዱ ክልል ውስጥ ማምረት የሚያስችል ብቸኛ የሆነ መብት ይሰጣል ። ፈቃዱ የማዕድን ሥራውን ለማካሄድ በቂ ይሆናል ተብሎ በሚገመት ደረጃ አስፈላጊ የሆነውን ክልል የሚሸፍን ይሆናል ፤ የክልሉ ወሰንና ቅርጽ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል ።

SECTION 2

SMALL-SCALE MINING

16. *Small-Scale Mining License*

1. A small-scale mining license grants an e right to mine for the minerals within the are fied in the license. The license shall cover t reasonably necessary to carry out mining op The form and boundary of the area shall be de ed boundary of the area shall be determined by directive issued by the Minister.

2. A small-scale mining license may be tran assigned or encumbered with the prior appr the Licensing Authority Subject to the provi Article 5 of this Proclamation, the license m be inherited, provided that no subdivision license area by partition shall result without th approval of the Licensing Authority and, p further, that suspension of mining operations the license for more than 90 days shall be for its revocation.

17. *Duration and Renewal*

1. A small-scale mining license shall be valid for mum period of ten years or the life of the whichever is shorter, and may be renewed maximum period of five years each subject article 2 of this Article.

2. The licensee shall have the right to renew the provided that he can demonstrate the continu nomic viability of mining the deposit, has fulfil obligations specified in the license and is breach of any provision of this Proclamation, tions or directives issued hereunder which con grounds for suspension or revocation of the lic

SECTION 3

LARGE-SCALE MINING

18. *Large-Scale Mining License*

1. A large-Scale mining license grants an exclusive to mine for the minerals within the area sp in the license. The license shall cover the area r ably necessary to carry out mining operations form and boundary of the area shall be deter by directive issued by the Minister.

፪. ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፡ ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስፈቀድ ለሌሎች ሊተላለፍ ፣ ሊዳረግ ወይም በዕዳ ሊያዝ ይችላል ። እንዲሁም የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ በውርስ ሊተላለፍ ይችላል ፤ ሆኖም ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳይፈቅድ ውርሱ የፈቃዱን ክልል መከፋፈልን የሚያስከትል ሊሆን አይችልም ፤ በተጨማሪም የማዕድን ሥራው በዚህ ምክንያት ከአንድ መቶ ሰማንያ ቀናት በላይ ተቋርጦ ቢቆይ ፈቃዱን ለመሠረዝ በቂ ምክንያት ይሆናል ።

ስለፈቃድ ዘመንና ዕድሳት

፩. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ቢበዛ ለሃያ ዓመት ወይም የክምችቱ ዕድሜ ከሀያ ዓመት በታች ከሆነ ለዚሁ ዘመን የሚያገለግል ይሆናል ። ፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ከአሥር ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል ።

ባለፈቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈጸመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል ።

ንዑስ ክፍል አራት

ስለ ማዕድን ውኃ ፣ ስለ ጂኦተርማል ክምችት እና ስለ ኮንስትራክሽን ማዕድናት

ስለማዕድን ውኃ እና ስለ ጂኦተርማል ክምችት

፩. ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው ፣ ሥፍራው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የተያዘ ወይም የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር ፣ የማዕድን ውኃን በይዞታው ሥር ከሚገኝ ሥፍራ ያለክፍያና ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን አስቀድሞ በማሳወቅ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አምርቶ መጠቀም ይችላል ፤ ሆኖም የአዋሳኝ ባለይዞታዎችን መሬት ወይም ንብረት አጠቃቀም ማወክ ወይም በእነዚሁ ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም ።

፪. የማዕድን ውኃን የሚመለከት የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የውኃው ምንጭ ተመልሶ ሊሞላ በሚችልበት መጠን እንዲሁም ውኃው ሊወጣበት የሚችለውን አግድም ጥልቀት ግምት ውስጥ በማስገባት የምርቱን ብዛትና በየጊዜው መመረት የሚገባውን መጠን ሊወስን ይችላል ፤ እንዲሁም ፈቃዱ ብራይንን የሚመለከት ሲሆን የማዕድናቱን አመራረትና አወጣጥ ሁኔታዎች እና የተረፈውን ውኃ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች ሊወስን ይችላል ።

2. A large-scale mining license may be transferred, assigned or encumbered with the prior approval of the Licensing Authority. Subject to the provisions of Article 5 of this Proclamation, the license may also be inherited, provided, that no subdivision of the license area by partition shall result without the prior approval of the Licensing Authority and, provided further, that suspension of mining operations under the license for more than 180 days shall be grounds for its revocation.

19. *Duration and Renewal*

1. A large-scale mining license shall be valid for a maximum period of twenty years or the life of the deposit whichever is shorter. The license may be renewed subject to sub-article 2 of this Article for a maximum period of ten years each.

2. The licensee shall have the right to renew the license, provided he can demonstrate the continued economic viability of mining the deposit, has fulfilled the obligations specified in the license and is not in breach of any provision of this Proclamation, regulations or directives issued hereunder which constitutes grounds for suspension or revocation of the license.

SECTION 4

MINERAL WATER, GEOTHERMAL DEPOSITS AND CONSTRUCTION MINERALS

20. *Mineral Water and Geothermal Deposits*

1. A legitimate occupant of land may produce and use for non-commercial purpose, without charge and with prior notification to the Licensing Authority, mineral water from the area he occupies, provided that the area is not reserved or excluded pursuant to Article 6 of this Proclamation and, provided further, that he does not disturb or damage the adjacent occupant's land or property.

2. The mining license of mineral water may specify the amount and rate of production, which shall generally be limited to that which permits the renewal of the water aquifer, and the horizon or depth from which the water may be extracted. The license of brines may specify conditions of production and of extraction and disposal of minerals produced and of the use and disposal of the water remaining.

፫. የጂኦተርማል ክምችትን የሚመለከት የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ሊወጣ የሚችለውን የውኃ መጠንና የካሎሪፊክ ይዘት ሊወስን ይችላል ፤ እንዲሁም ተረፈ ምርቶች ስለሚለዩበትና ስለሚወገዱበት ፣ ስለውሃው አመራረት አጠቃቀምና ክምችቱን ለመጠበቅ ስለሚደረግ የውኃ መልሶ ማስገባት ሁኔታዎች ሊወሰን ይችላል ።

፳፩. ስለ ኮንስትራክሽን ማዕድናት

፩. ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው ፣ ሥፍራው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የተያዘ ወይም የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር ፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በይዞታው ሥር ከሚገኝ ሥፍራ ያለክፍያና ፈቃድ ሳያስፈልገው ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አምርቶ ለመጠቀም ይችላል ፣ ሆኖም የአዋሳኝ ባለይዞታዎችን መሬት ወይም ንብረት አጠቃቀም ማወክ ወይም በእነዚሁ ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም ።

፪. ማንኛውም ሰው ለንግድ ላልሆነ ዓላማ መንገዶችን፣ ግድቦችን ፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ፣ ትምህርት ቤቶችን ፣ ሆስፒታሎችንና የንግድ ያልሆኑ ሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ሥራዎችን ለመሥራትና ለመጠገን ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን ስምምነት በቅድሚያ በማግኘት የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ያለክፍያ ማምረትና መጠቀም ይችላል ።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚካሄድን የኮንስትራክሽን ማዕድናት የማምረት ሥራ በተመለከተ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ እና አንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

ምዕራፍ አራት
ስለባለፈቃዶች መብትና ግዴታ

፳፪. ስለመሬት ይዞታና አጠቃቀም

፩. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ላይ ወደተመለከተው ክልል ለመግባትና የፈቃዱ ዘመን እስከሚያበቃ ባለይዞታ ሆኖ መቆየት ይችላል ።

፪. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል ውስጥ ለማዕድን ሥራዎች ድጋፍ የሚያደርጉ ሥራዎችን ማካሄድ እንዲሁም ለራሱ ፣ ለወኪሎቹ ፣ ለሠራተኞቹና ለጥገኞቻቸው ፍጆታ የሚውል ሰብል ማልማትና ከብት ማርባት ይችላል ።

፫. የአነስተኛ ደረጃ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ አግባብ ካለው አካል ከፈቃዱ ክልል ውጭ ለሥራው የሚያስፈልገውን ሥፍራ በኪራይ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል ። የኪራዩ ውል ግዴታዎች በሚመለከተው አካል የሚወሰን ሆኖ የሚጸናበት ዘመንም ግን የእድሳው ጊዜ ከማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃዱ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል ።

3. The mining license of geothermal deposit may [cut off]
the volume of water and the calorific content w[cut off]
may be extracted, it may also fix conditions o[cut off]
extraction and disposal of by-products and o[cut off]
production, use and reinjection of water in ord[cut off]
preserve the deposit.

21. *Construction Minerals.*

1. A legitimate occupant of land, may produce and [cut off] for non commercial purpose, free of charge and w[cut off] out permission of the Licensing Authority, cons[cut off] tion minerals from the area he occupies, provided [cut off] the area is not reserved or excluded pursuant [cut off] Article 6 of this Proclamation and, provided fu[cut off] that he does not disturb or damage the adj[cut off] occupant's land or property.

2. Any person may produce and use for non-comm[cut off] purpose without charge and with prior permissi[cut off] the Licensing Authority, construction minerals fo[cut off] construction and maintenance of roads, dams, air[cut off] schools, hospitals and other non-commercial p[cut off] works.

3. The provisions of Articles 24 and 26 sub article[cut off] and (4) of this Proclamation shall apply to mining operation of construction minerals cond[cut off] pursuant to sub article (2) of this Article.

CHAPTER 4
RIGHTS AND OBLIGATIONS OF LICENSEE

22. *Possession and use of land*

1. The licensee may enter and occupy the land cove[cut off] the license during its term.

2. The licensee may use the land of the license ar[cut off] activities in support of mining operations and [cut off] grow crops and graze livestock for the consumpt[cut off] himself, his agents and employees and their [cut off] dents.

3. The holder of a small-scale or a large-scale [cut off] license may also request the appropriate autho[cut off] lease for land outside of the license area whi[cut off] required for mining operations. The terms an[cut off] ditions of such lease shall be determined by the [cut off] priate authority and its duration shall be the [cut off] as that of the license including any renewals [cut off]

በኮንስትራክሽን ማዕድናት ፣ በውኃ እና በደን ውጤቶች ስለመጠቀም

፩. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል የሚገኙ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በሚመለከት ለሌላ ሰው ፈቃድ ተሰጥቶባቸው ካልሆነ በስተቀር እነዚህኑ ማዕድናት ለማዕድን ሥራው በሚያስፈልገው መጠን ማውጣትና መጠቀም ይችላል ።

፪. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል የሚገኘውን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃ ለራሱ ፣ ለወኪሎቹ ፣ ለሠራተኞቹና ለጥገኞቻቸው ፍጆታ መጠቀም ይችላል ። እንዲሁም ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያስፈልገውን የውኃ መጠን በከፍተኛ ደረጃ የማይቀንስና መመሪያን ተከትሎ በሌላ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር የውኃ ብክለትን የማያስከትል እስከሆነ ድረስ ለማዕድን ሥራዎች አገልግሎት በገጸ ምድር ውኃ ሊጠቀም ይችላል ። ባለፈቃዱ በቅድሚያ አግባብ ካለው የመንግሥት ባለሥልጣን ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በውኃ መፋሰሻዎች ላይ ግድብ መሥራት ወይም አቅጣጫቸውን መቀየር አይችልም ።

፫. የምርመራ ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆኑ የደን ውጤቶችን ከፈቃዱ ክልል መቁረጥና መጠቀም ይችላል ። ባለፈቃዱ የደን ውጤቶችን ስለመቁረጥና በምትካቸው ችግኞችን ስለመትከል የወጡ አግባብ ያላቸው ሕጎች ማክበርና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት ደኑን መልሶ ለማልማት የሚያስችል ዕቅድ ማቅረብ አለበት ።

፬. የፍለጋ ወይም ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ሥራው ወደሚካሄድበት ሥፍራ ለመድረስ አስፈላጊ የሆነውን መንገድ ለማውጣት የግድ መቆረጥ ያለባቸውን ዛፎች ብቻ መቁረጥና መጠቀም ይችላል ።

ስለሌሎች ባለይዞታዎች

፩. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል ፣ በተከራየው መሬትና አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያላቸውን ሰዎች ጣልቃ በመግባት ላለማወክ ተገቢውን ጥንቃቄ ይወስዳል ።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የባለፈቃዱ የማዕድን ሥራዎች ሌላ ባለይዞታ ከሥፍራው እንዲነሳ የሚያስገድዱ ከሆነ ባለፈቃዱ የሚነሳው ሰው ሊከፈለው ስለሚገባው ካሣ ስምምነት ላይ ለመድረስ መሞከር አለበት ። ባለይዞታው ከሥፍራው ለመነሳት ወይም በካሣው መጠን ላይ ለማስማማት ፈቃደኛ ሳይሆን ቢቀር ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ለባለፈቃዱ ሥራ ሲባል ባለፈቃዱ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የሚወሰነውን ካሣ ከፍሎ ባለይዞታው የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለው እንዲለቀቅና ከሥፍራው እንዲነሳ ሊያደርግ ይችላል ። ለዚህ ጉዳይ አፈጻጸም ሲባል የማዕድን ሥራ በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ ፩ሺ፬፻፷ መሠረት «የሕዝብ አገልግሎት ሥራ» ሆኖ ይቆጠራል።

23. Use of construction minerals, water and timber

1. The licensee may remove and use construction minerals required for mining operations which are found within the license area or within the land covered by a lease, provided that no other license has been issued to another person for such minerals.

2. The licensee may use surface and subsurface water found in the license area and the area of a lease for the consumption of himself, his agents, employees and their dependents. A licensee may also use surface water for mining operations, provided that such use does not result in the substantial reduction of the amount of water needed by other users or, unless authorized pursuant to directive, result in the pollution thereof. A licensee shall not construct a dam or divert any watercourse without the prior approval of the appropriate government authority.

3. The holder of an exploration, small-scale or large scale mining license may cut and use, from the license area and the area of lease, timber which is necessary for mining operations. The licensee shall comply with the applicable laws regarding the cutting of timber and reforestation and must submit a restoration plan as may be specified by directive.

4. The holder of prospecting license or an artisanal mining license shall cut and use only such timber as is strictly necessary for access to the areas in which mining operations are carried out.

24. Other Occupants

1. The licensee shall take proper precaution not to interfer with the other legitimate occupants of the license area, the land covered by a lease and adjacent land.

2. Notwithstanding the provision of sub-trticle 1 of this Article, if the licensee's mining operations require that the other occupant be displaced, the licensee shall attempt to negotiate the compensation payable to such occupant. If the occupant refuses to be displaced or to agree on the amount of compensation, the Licensing Authority may cause the expropriation of immovable property, if any, and the eviction of such occupant on behalf of the licensee's mining operations, subject to the licensee's payment of compensation determined by the Licensing Authority. In this connection, mining operations shall be deemed a public purpose within the meaning of Article 1460 of the Civil Code of Ethiopia.

፫. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል ፣ በተከራየው መሬት ወይም አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያለውን የሌላ ሰው ግንባታ ንብረት ካበላሸ ፣ ካጠፋ ወይም ጉዳት ካደረሰ ላደረሰው ብልሽት ፣ ጥፋት ወይም ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ይከፍላል ።

፳፭. <u>ስለ መሠረተ ልማት አውታሮችና ስለሌሎች ግንባታዎች</u>

፩. የምርመራ ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በፈቃዱ ክልልና በተከራየው መሬት ላይ መንገዶችን ፣ የመገናኛ መሥመሮችንና የኃይል ማመንጫዎችን ጨምሮ ለሥራው የሚያስፈልጉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት ፣ ማካሄድና በአግባቡ መጠበቅ ይችላል ። ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ከሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በመመካከር አስቀድሞ ሲፈቅድለት ባለፈቃዱ እነዚህን የመሠረተ ልማት አውታሮች ከፈቃድና ከተከራየው መሬት ክልል ውጭም መገንባት ይችላል ።

፪. ባለፈቃዱ ሌሎች ሰዎች እንዳይገለገሉባቸው መሰናክል የማይፈጥር እስከሆነ ድረስ በነባር የመሠረተ ልማት አውታሮች ሊገለገል ይችላል ።

፫. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ለሚመለከታቸው ሰዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሆነው ሲያገኛቸው ባለፈቃዱ ከሌላ ባለፈቃድ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ለሚጠቀምባቸውና በፈቃዱ ክልል ወይም በተከራየው መሬት ላይ ለሚዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታና ጥገና እንዲተባበርና ገንዘብ እንዲያወጣ ማድረግ ይችላል ። የግንባታውና የጥገናው ወጪ ድልድል በተጠቃሚዎቹ የንፍስ ወከፍ ግልጋሎት መጠን ላይ ተመሥርቶ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ይወሰናል ።

፬. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በባለፈቃዱ የማዕድን ሥራ ላይ እንቅፋት የማይፈጥርበት እስከሆነ ድረስ ባለፈቃዱ በዘረጋቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙ እንዲፈቅድ ማድረግ ይችላል ።

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በመሠረተ ልማት አውታሮቹ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ሰው ለንግድ ሥራ የሚገለገልባቸው ከሆነ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ለባለፈቃዱ የሚሰጠውን ክፍያ ሊወስን ይችላል ። የክፍያው መጠን የሚወሰነው የተባለው ሰው የሚያገኘውን ግልጋሎት ሌሎች ሰዎችና ባለፈቃዱ በመሠረተ ልማት አውታሮቹ በመጠቀም ከሚያገኙት ግልጋሎት ድምር ውጤት ጋር በማመዛዘን ይሆናል ።

፮. ድንገተኛ ወይም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሲፈጠር በመሠረተ ልማት አውታሮቹ ላይ ለሚደርሰው ብልሽት ካሣ በመክፈል ሌሎች ሰዎች ወይም መንግሥት በጊዜያዊነት እንዲገለገሉባቸው እንዲፈቅድ መንግሥት ባለፈቃዱን ማስገደድ ይችላል ።

3. A Licensee shall, if he damages, injures or destroys any installations or other property of another legitimate occupant of the license area, the land covered by a lease or adjacent land, pay to the occupant compensation representing the value of such damage, destruction or injury.

25. *Infrastructure and other Construction*

1. The holder of an exploration, small-scale or large-scale mining license may construct, operate and maintain within the license area and the area covered by a lease all infrastructure necessary for operations including facilities for roads, communications and power. The licensee may also, with the prior approval of the Licensing Authority and in consultation with other authorities of the Government, construct such facilities outside of the areas covered by the license and a lease.

2. The licensee may use the existing infrastructure if their use by such licensee shall not impair the use thereof by other persons.

3. The Licensing Authority may require the licensee to cooperate and contribute financially in the construction and maintenance of infrastructure to be used jointly with another licensee or other persons within the areas covered by his license or lease if such infrastructure is to the economic benefit of the persons concerned. The allocation of the costs of construction and maintenance of such infrastructure shall be determined by the Licensing Authority on the basis of proportional use.

4. The Licensing Authority may require the licensee to permit other persons to use infrastructure of the licensee, provided that such use does not impede mining operations.

5. The Licensing Authority may impose on such person stated under sub-article 4 hereof a fee payable to the licensee if the use of such infrastructure is not for a non-commercial purpose. The fee imposed shall be based on the extent of that person's use in proportion to the total use of such infrastructure by all other such persons and the licensee.

6. In circumstances of urgency or national emergency, the Government may also require the licensee to permit another person or the Government to use temporarily the infrastructure of the licensee, subject only to the payment of compensation in the event of damage thereto.

፯. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ክልል ወይም በተከራየው መሬት ላይ ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆኑ የኢንዱስትሪ ፣ የአስተዳደር ፣ የመኖሪያ ፣ የሕክምናና ሌሎች ሕንፃዎችንና መገልገያዎችን ሊገነባ ይችላል ።

፰. የፍለጋ ፣ ለምርመራ ወይም ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዱ የሚያካሂዳቸው የግንባታ ሥራዎች የጊዜያዊነት ጠባይ ያላቸው መሆኑና የፈቃዱ ዘመን ከመፈጸሙ ወይም ግንባታዎቹ የሚገኙበት ክልል ከመለቀቁ በፊት መነሳት አለባቸው።

፱. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፪/፪/ ቢኖርም ፣ በአነስተኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የተሠሩ የቋሚነት ጠባይ ያላቸው የግንባታ ሥራዎች የፈቃዱ ዘመን ሲፈጸም ባለፈቃዱ ሊያነሳቸው ወይም ከተዋቸውም መንግሥት ያለ ምንም ክፍያ ወስዶ የራሱ ንብረት ሊያደርጋቸው ይችላል ።

ስለማዕድን ሥራዎች አፈጻጸም

ባለፈቃዱ ፣

፩. የማዕድን ሥራውን በፍጥነት መጀመር እና ጥንቃቄ ፣ ትጋትና ቅልጥፍና በተሞላበት ሁኔታ ተገቢ በሆነ ቴክኖሎጂና በማዕድን ኢንዱስትሪ ተቀባይ ነት ባገኘ የአሠራር ልምድ መሠረት ማካሄድ አለበት ፤

፪. በሥራ ዕቅዱና በወጪ ግዴታው መሠረት ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል ፣ ሆኖም ግን በተለየ ሁኔታ እንዲሠራ የሚያስገድደው በቂ ምክንያት ሲኖረውና ይህም በቅድሚያ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲፈቅድ ከሥራ ዕቅድና ከወጪ ግዴታው ውጭ ሊሠራ ይችላል ። እንዲሁም ሲሆን አስፈላጊ ያልሆኑ ሥራዎችን ከመሥራትና ወጪዎችን ከማውጣት መቆጠብ አለበት ፤

፫. የወኪሎቹን ፣ የሠራተኞቹንና የሌሎች ሰዎችን ጤንነትና ደኅንነት በሚያረጋግጥ እና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ወይም ብክለን በተቻለ መጠን መከላከል በሚያስችል ሁኔታ ሥራውን ማከናወን አለበት ፤

፬/ የማዕድን ሥራዎቹን ለሥራው ተፈጻሚነት ባላቸው ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ማካሄድ አለበት ።

ስለቅጥር ፣ ስለሥልጠናና ስለሀገር ውስጥ አቅርቦት

ማንኛውም ባለፈቃድ ፣

፩. ተፈላጊው ችሎታ ላላቸው ኢትዮጵያውያን የቅጥር ቅድሚያ ይሰጣል ፤

፪. ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆነ ሥልጠናና ትምህርት ለሠራተኞች ይሰጣል ፤ እንዲሁም አግባብ ያላቸውን የስልጠና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል ፤

፫. በዋጋቸው ተወዳዳሪ እና በጥራታቸው ተመጣጣኝ ደረጃ ያላቸው እንደልብ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ቅድሚያ ይሰጣል ።

7. The licensee may construct within the area covered by the license or a lease all industrial, administrative, residential, medical and other buildings and facilities necessary for mining operations.

8. All construction by the holder of a prospecting, an exploration or an artisanal mining license shall be of a temporary nature and shall be removed prior to the termination of the license or to the relinquishment of the area on which such construction is located.

9. Notwithstanding the provisions of Article 52 (2) of this Proclamation, all constructions of permanent nature built by a holder of a small-scale or large-scale mining license may, upon the termination of the license, either be removed by the licensee or be abandond and become the property of the Government free of charge.

26. *Conduct of Mining Operations*

The licensee shall:

1. promptly commence and carry out mining operations in a prudent, diligent and efficient manner, in accordance with appropriate technology and good practices generally accepted in the mining industry;

2. comply with all work programmes and expenditure obligations unless a departure there from is justified and receives the prior approval of the Licensing Authority, and avoid the performance of work or the incurring of expenditure which is not required;

3. conduct mining operations in such a manner as to ensure the health and safety of his agents, employees and other persons, and to minimize damage or pollution to the environment; and

4. conduct mining operations in accordance with applicable regulations and directives.

27. *Employment, Training and Local Supply*

The licensee shall,

1. give preference to the employment of Ethiopian nationals, provided that such persons have the required qualifications;

2. give employees the training and education necessary for mining operations and comply with appropriate training programs;

3. give preference to domestic goods and services, where they are readily available at competitive prices and are of comparable quality.

፳፰· ፈቃድ የተጠየቀባቸውን ሥፍራዎች ስለመከለል

፩· የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ፈቃድ የጠየቀበትን ሥፍራ ወሰን ኦፊሴላዊ በሆነ ቅያስ ማሳየት አለበት ይህ ግዴታ ለመሬት ኪራይ በሚቀርብ ማመልከቻ ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል ።

፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ፣ ፲፫/፫/ ወይም ፴፩ መሠረት የፈቃድ ክልሉ ወይም የኪራይ ይዞታው ሲሻሻል ባለፈቃዱ በተደረገው ለውጥ መሠረት የሥፍራውን ወሰኖች ኦፊሴላዊ በሆነ ቅያስ ወዲያውኑ ማሳየት አለበት ።

፳፱· ስለመዛግብትና ሪኮርድ እና ሪፖርት

ባለፈቃዱ ፤

